በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የህብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ

የ2005 ዓ/ም የ20/80 እና 40/60 ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር ለማደራጀት የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 144/2015

ግንቦት/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>መመሪያ ቁጥር 144/2015</u>

<u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ የ2005 ዓ.ም የ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀትና የአፈጻጸም መመሪያ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2005 ዓ/ም በ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተመዝግበው እየቆጠቡ በመረጃ ቋት ውስጥ ከሚጠባበቁት ተመዝጋቢዎች መካከል አቅም ያላቸውንና ፈቃደኛ የሆኑትን ፤በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ በኩል የተለዩትን በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ለማደራጀት እንዲያስችል ግልጽ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ተደራጅተው የቤት ችግራቸውን ለመቅረፍ እንዲችሉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተቀመጠውን መመዘኛ ሊያሟሉ የሚችሉትን ቤት ፈላጊዎች ግልፅ ፣ተደራሽ ፣አሣታፊ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት መፍጠር በማስፈለጉ፤

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አዉጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

አጠቃላይ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የ2005 ዓ.ም የ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀትና የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 144/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. አዋጅ"ማለት እንደ አግባብነቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 985/2009 ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋ ቁጥር 74/2014 ነው፤
4. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው፤
5. "ኤጀንሲ"ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ሲሆን እስከ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ያለውን መዋቅር ይጨምራል፤
6. "አደራጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ሲሆን እስከ ክፍለ ከተማ ያለውን መዋቅር ይጨምራል፤
7. "የኅብረት ሥራ ማኅበር " ማለት በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የጋራ ህንፃ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፤
8. "ዝግ ሂሳብ" ማለት የመኖሪያ ቤት ለመሥራት በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስም ቅድሚያ የሚጠበቅበትን የቤቱን ግንባታ ወጪ በባንክ ለማስቀመጥ የሚከፈት የማይንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ ነው፤
9. "ባንክ" ማለት የኅብረት ስራ ማኅበራቱ ገንዘባቸዉን በማይንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ ለማስቀመጥ ወይም ሌሎች የባንክ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚመርጡት የመንግሥት ወይም የግል ባንክ ነው፤

10. "የቤት ልማት ፕሮግራም "ማለት በከተማ አስተዳደሩ አስተባባሪነት የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ የተዘጋጀ የ20/80 እና 40/60 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፤
11. "የለማ መሬት" ማለት መሠረተ ልማት የተሟላለት እና ከማንኛውም ከይገባኛል ጥያቄ ነጻ የሆነ መሬትነዉ፤
12. "መረጃ ቋት"ማለት በ20/80 እና በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም በ2005 ዓ.ም በከተማ አስተዳደሩ ስልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግበው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቁጠባቸውን ያላቋረጡ ማለት ነው፡፡
13. "ተጠባባቂ"ማለት በመረጃ ቋት ውስጥ ያሉና በእጣ ድልደላ ጊዜ እድል ያላገኙና ሌላ እድል በመጠባበቅ ላይ ያሉ ማለት ነው፤
14. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2005 ዓ.ም በ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝግበው በመረጃ ቋት ውስጥ ካሉት ተመዝጋቢዎች መካከል በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ለመደራጀት ፈቃደኛ ሆነው በቢሮው በተለዩት ተደራጆችና ይህን መመሪያ በሚያስፈጽም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. **ዓላማ**

በቤት ልማት ፕሮግራም ከተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች አቅምና ፍላጎት ያላቸው በኅብረት ስራ ማኅበራት ተደራጅተው ገንዘባቸውን ፣እውቀታቸውን፣ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን በማቀናጀት የቤት ችግሮቻቸውን በጋራ ጥረት ሊፈቱ የሚችሉበትን አማራጭ መፍጠር ነው፡፡

6. **መርህ**

በአዋጁ የተጠቀሱት የኅብረት ሥራ ማኅበራት መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉት የዚህ መመሪያ መርሆች ይሆናሉ፡-

1. መሥፈርቱን በማሟላት በኅብረት ሥራ ማኅበር የሚደራጁ አባላት ግዴታቸውን እስካሟሉ ድረስ ያለምንም ልዩነት በእጣ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ፍትሃዊ፣ግልጽ እና የተጠያቂነትን አሰራር ማስፈን፤
2. የመኖሪያ ቤት ችግርን በራስ አቅም ለመፍታት የሚደረግ የእውቀት፣ የሀብትና ጉልበት አስተዋጽኦን የሚደግፍና የሚያበረታታ አቅጣጫን መከተል፤
3. በኅብረት ሥራ ማኅበር የሚደራጁ አባላት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደርያ ደንብና ውስጠ ደንብ መሠረት በሚወሰን ውሳኔ የመገዛት ግዴታ እና የመሳተፍ መብታቸው እንዲጠበቅ በማድረግ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የተላበሱ እንዲሆን ማስቻል፤
4. በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት የቤት ልማት ፕሮግራም ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማረጋገጥ፡፡

ክፍል ሁለት

የሕብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት

8. **ተጠቃሚዎችን ስለመለየት**

ቢሮው በ2005 ዓ/ም በ20/80 እና በ40/60 በቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን ተመዝግበው ስማቸው በምዝገባ መረጃ ቋት ውስጥ የሚገኙና በኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተው በራሳቸው አቅም ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸውን ተመዝጋቢዎች ቢሮው ባዘጋጀው መስፈርት መሰረት ተለይተው ለኤጀንሲው የተላኩትን ዝርዝር በመፈተሽ ይረጋገጣል፡፡

9. **የአደረጃጀት ሂደት**

1. ተደራጅ ቀደም ሲል በተመዘገበበት ወይም እንደ አዲስ በመረጠው የቤት ዓይነት መሠረት ቢሮው መረጃ በማደራጀት ለአደራጁ አካል በሚልከው መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፤
2. የቤት አይነት ምርጫ ያከናወነ እና በማኅበር ለመደራጀት እጣ የወጣለት ተደራጅ በአካል ቀርቦ በአደራጁ አማካይነት ይደራጃል፤

3. የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለምዝገባ ሲቀርቡ ከቤት ፍላጎት ምዝገባ ቅጻ-ቅጾች በተጨማሪ በኅብረት ሥራ አዋጅ አንቀጽ 10 (2) የተዘረዘሩትን እና በተለያዩ ቦታዎች ማኅበሩን ወክለው የሚንቀሳቀሱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አካላትን ውክልና ጭምር የያዘ ሰነድ ለአደራጁ ማቅረብ አለባቸው፤

4. የክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት በሚያቀርበው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መነሻ በማድረግ በአንድ ማህበር የሚደራጁ አባላት አዋጅና መመሪያውን በማይጥስ መልኩ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤

5. ማንኛውም ተደራጅ በማህበር ሲደራጅ የቤቱን የግንባታ ወጪ ቅድመ ክፍያ ለባንክ በማህበሩ ስም በተከፈተ ዝግ ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፤ገቢ ያደረገበትንም ማስረጃ በማህበሩ አማካኝነት ለአደራጁ አካል ያቀርባል፤

6. ማህበሩ ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን አሟልቶ ሲገኝ የክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ለባንክ በአባላቱ ስም ዝርዝር መሠረት በማህበሩ ስም ዝግ ሂሳብ እንዲከፈት ደብዳቤ ይጽፋል፤

7. በባንክና የክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (5) የተመለከተው ቅድመ ክፍያ የተቀበለው ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (6) መሰረት የተፃፈለትን ደብዳቤ ቁጥር፣ገቢ የተደረገውን የገንዘብ መጠን፣ገንዘቡን ገቢ ያደረገበትን የገንዘብ መቀቢያ ሰነድ ቁጥር እና ቀን ጠቅሶ ለአደራጁ አካል ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ደብዳቤ ይጽፋል፤

8. የክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (5) መሰረት ገንዘቡ ገቢ የተደረገበትን ማስረጃ ከማህበሩ ተወካዮች እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (6) መሰረት ከባንኩ የተፃፈለት ደብዳቤ ሲደርሰው ማኅበሩን መዝግቦ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

9. የክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ማህበሩ ሲደራጅ የግንባታ ወጪውን 70% (ሰባ በመቶ) በማህበሩ ስም ለባንክ ገቢ ማድረጉን በማረጋገጥ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበሩን አስፈላጊ የምዝገባና የባንክ ሂሳብ ሠነዶችን በማያያዝ ማህበሩ መሬት እንዲመቻችለት ለቢሮ ደብዳቤ ይጽፋል፤

10. ቀሪውን 30% (ሠላሳ በመቶ) የግንባታ ወጪ በማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ከባንክ ጋር በሚፈጠር የብድር ስምምነት መሠረት ውል ለመግባት ፈቃደኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

10. **<u>የኅብረት ስራ ማኅበር አባላት ብዛት</u>**

የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ማህበር አባላት ብዛት እንደ ቤቱ ዓይነት በቢሮው ተወስኖ በሚላከው መሰረት ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የተለያዩ አካላት ተግባር፣ ግዴታና ኃላፊነት</u>

11. **<u>የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበር አባላት ግዴታና ኃላፊነት</u>**

በጋራ ህንጻ ቤት ለመስራት የተደራጀ አባል የሚከተሉት ግዴታና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. በጋራ ህንጻ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ለመመዝገብና ለመደራጀት የሚፈልግ ማንኛውም ተደራጅ ይህን መመሪያ የማክበር፤
2. ማንኛውም ተመዝጋቢ ቀደም ሲል በተመዘገበበት ወይም እንደ አዲስ በመረጠው የቤት ዓይነት መሠረት በእጣ በተደለደለበት የጋራ መኖሪያ ህንጻ ህብረት ስራ ማህበር በመደራጀት የቤቱን ግንባታ ወጪ በህብረት ስራ ማህበሩ ስም በተመረጠው ባንክ በተከፈተ ዝግ ሂሳብ ገቢ የማድረግ፤
3. በኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጅ አባል የህንጻ ግንባታው ሳይጠናቀቅ ወይም በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን የሚቀበል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበሩ አባል በሞት ምክንያት ሲለይ በሕግ አግባብ ተረጋግጦ ለሚቀርበው ወራሽ ሊተላለፍ ይችላል፤
5. ማንኛውም አባል ከዚህ መመሪያ ውጭ ከምዝገባ፣ከአደረጃጀትና ከቤት ማስተላለፍ ጋር በተያያዘ በአባላት ለሚፈጸሙ ሕገወጥ ድርጊቶች በጋራም ሆነ በተናጠል ኃላፊነት የመውሰድ፤
6. ማንኛውም የህብረት ስራ ማኅበር አባል ከዚህ መመሪያ ውጭ የተፈጸሙና

የሚፈጸሙ ማናቸውንም ሕገወጥ ድርጊቶችን ለቢሮው እና ለአደራጁ አካል የመጠቆም፤

7. የህብረት ስራ ማህበሩ አባላት የቤቶችን ግንባታ በቅርብ በመከታተል በገንዘብ፣ በእውቀትና በጉልበት የመደገፍ፤
8. የቤቶቹ ግንባታ ሲጠናቀቅ በቦታው በመገኘት የጋራ ህንጻ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማኅበሩ አማካኝነት አባል ወይም ሕጋዊ ወኪል በተገኘበት በእጣ የሚደርሰውን ቤት የመረከብ፤
9. ማንኛውም የህብረት ስራ ማህበር አባል በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 7 በተመላከተው መሰረት ከአባልነት በሚሰረዝበት ጊዜ በምትኩ ከምዝገባ ቋት ውስጥ ቢሮው በሚልከው መሰረት የሚተካ መሆኑን የመቀበል፤
10. አባሉ ሕገ-ወጥነትንና ያልተገባ ተጠቃሚነትን ለመከላከል ይቻል ዘንድ አሻራ ለመውሰድ በሚወጣው ፕሮግራም መሠረት ቀርቦ አሻራ የመስጠት፤
11. በማህበሩ ስም በዝግ ሂሳብ ከሚቀመጠው ገንዘብ ግንባታ ለማስጀመር 40%፤ በቀጣይ ቢሮው በሚያረጋግጠው የግንባታ ደረጃ መሰረት በየዙሩ 10% የሚለቀቅ መሆኑን የሚቀበል፡፡

12. <u>የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማኅበር ግዴታና ኃላፊነት</u>

ማኅበሩ የሚከተሉት ግዴታና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ቀደም ሲል በተመዘገቡበት ወይም እንደ አዲስ በመረጡት የቤት ዓይነት መሠረት በማህበር እንዲደራጁ እጣ የወጣላቸውን ተደራጆች በማህበር የመደራጀት ሂደት ያስተባብራል፤
2. እያንዳንዱ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ህገ-ወጥነትንና ያልተገባ ተጠቃሚነትን ለመከላከል እንዲቻል በሚደረገው ምዝገባ ኘሮግራም መሠረት ቀርቦ መመዝገብና አባላቱንም ማስመዝገብ ይኖርበታል፤
3. የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩን የመመስረቻ ቃለ-ጉባኤ፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አዘጋጅቶ ለአደራጁ አካል የማቅረብ፤
4. አባላትን በመወከል ከምዝገባ ጀምሮ ያሉትን የዝግ ቁጠባ ሂሳብ ፣የመሬት፣

የግብዓትና ከማህበሩ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን የማቅረብና የማስፈጸም፤

5. የእያንዳንዱን አባል በህብረት ስራ ማህበሩ ስም ገንዘቡን በዝግ ሂሳብ ገቢ የማድረግ፣ገቢ ያደረገበትንም ማስረጃ ለአደራጁ አካል የማቅረብ፤
6. የቤቶቹ ግንባታ በተቀመጠው ዲዛይንና በውሉ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን የመከታተልና የመቆጣጠር፤
7. የቤቶች ግንባታ መጠናቀቁን በማረጋገጥ አባላት ቤታቸውን በእጣ እንዲረከቡ የማመቻቸት፤
8. የአባላትን እና የማህበሩን መብትና ጥቅም ለማስከበር ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በትብብር የመስራት፤
9. እያንዳንዱ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበር የአባላቱን አሻራ ለመውሰድ በሚወጣው ፕሮግራም መሠረት ቀርቦ አሻራ እንዲሰጡ የማድረግ፤
10. የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበሩ አባላትን ከምዝገባ ቋት መሰረዛቸውን የሚያሳይ ማስረጃ የመያዝ፤
11. ስለ አካል ጉዳተኞች እና ሴቶች ልዩ ተጠቃሚነት በሌሎች ህጎች የተደነገጉ ህጎችን ተፈጻሚ የማድረግ፡፡

13. ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ኃላፊነትና ተግባር

ኤጀንሲው በአዋጁ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. በ20/80 እና በ40/60 የመኖሪያ ቤት ፕሮግራም ከተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች መካከል በፍላጎት ወደ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የሚመጡትን ተመዝጋቢዎች 2005 ዓ.ም በተመዘገቡበት ወይም እንደ አዲስ በመረጡት የቤት ዓይነት ፕሮግራም የተመዘገበውን መረጃ ከቢሮ የመቀበል፤
2. ስለ መኖሪያ ቤቶች ህብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት ይዘትና አስፈላጊነት እንዲሁም ስለ አመዘጋገብ ስርዓት በቂ መረጃ የመስጠት፤
3. ማንኛውም ማህበር ለምዝገባ ብቁ እስከሆነና የምዝገባ መስፈርቱን አሟልቶ በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሉ እስከቀረበ ድረስ በመመዝገብና በማረጋገጥ

አደራጅቶ ህጋዊ እውቅና የመስጠት፤

4. በማህበሩ ስም ፋይል የመክፈት፣ በማህበሩ የተሞሉትን ቅጻቅጾች በአግባቡ የማደራጀትና የመያዝ፤
5. ማህበሩ ሲደራጅ የግንባታ ወጪውን 70% (ሰባ በመቶ) በማህበሩ ስም ለባንክ ገቢ ማድረጉን በማረጋገጥ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበሩን አስፈላጊ የምዝገባና የባንክ ሂሳብ ሠነዶችን በማያያዝ ማህበሩ መሬት እንዲመቻችለት ለቢሮ መረጃ አደራጅቶ በጽሁፍ የመስጠት፤
6. ማህበራት ቅድመ ሁኔታውን አሟልተው ሲቀርቡ የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው አካል የመጻፍ፤
7. ማህበራት ተመዝግበው እውቅና ስለማግኘታቸው የሚያስረዳ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃ የመስጠት፤
8. ማህበሩ የተሰጠው ቦታ ለተደራጀበት ዓላማ መዋሉን ክትትልና ድጋፍ የማድረግ፤
9. ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ ለማህበሩ የመስጠት፤
10. ማንኛውም ተደራጅ በማህበር ሲደራጅ የቤቱን የግንባታ ወጪ ቅድመ ክፍያ ለባንክ በማህበሩ ስም በተከፈተ ዝግ ሂሳብ ገቢ አድርጎ፣ገቢ ያደረገበትንም ማስረጃ በማህበሩ አማካኝነት ሲያቀርብ የመቀበል፤
11. ለማህበር መሬት ከመሰጠቱ በፊት እጣ የወጣለት ተመዝጋቢ ከ20/80 ወይም ከ 40/60 ፕሮግራም የመረጃ ቋት መሰረዙን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከቢሮ ይቀበላል፤
12. ማህበሩ ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን አሟልቶ ሲገኝ ለባንክ በአባላቱ ስም ዝርዝር መሠረት በማህበሩ ስም ዝግ ሂሳብ እንዲከፈት ደብዳቤ የመጻፍ፤
13. ከባንክ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ክፍያ የተቀበለው ባንክ የተፃፈለትን ደብዳቤ ቁጥር ፣ገቢ የተደረገውን የገንዘብ መጠን፣ገንዘቡን ገቢ ያደረገበትን የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር እና ቀን ጠቅሶ እንዲልክለት የመጠየቅና መረጃውን የማደራጀት፤
14. በዝግ ሂሳብ ከተቀመጠው የማህበሩ ገንዘብ ለግንባታና ለልዩ ልዩ ክፍያዎች ቢሮ ሲጠይቅ አሰራሩን ጠብቆ እንዲለቀቅ ለባንክ ደብዳቤ የመጻፍ፤

15. ማህበሩ በልዩ ልዩ ምክንያት ቢፈርስ በዝግ ሂሳብ የተያዘው ገንዘብ እንዲመለስ በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰንና ሲጠየቅ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት የማስፈጸም፤

16. በዚህ አንቀጽ የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው ይህንን መመሪያ በተገቢው ለማስፈጸም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት የመስራት፤

17. ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በአዋጁ ላይ የተመለከቱ ሌሎች ተግባራትንና ኃላፊነቶችን ይወጣል፤ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

14. የባንክ ተግባርና ኃላፊነት

1. በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም በዝግ ሂሳብ ገንዘብ ለማስቀመጥ አካውንት እንዲከፈት በአደራጅ መስሪያ ቤት ሲጠየቅ በስምምነቱ መሠረት የመክፈት፤

2. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በእያንዳንዳቸው ስም የግንባታውን ወጪ በማህበሩ ስም በተከፈተው ዝግ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረጋቸውን በማረጋገጥ ለአደራጅ የማሳወቅ፤

3. በአደራጁ አማካኝነት ለህብረት ስራ ማህበሩ በዝግ ሂሳብ ከተያዘው ገንዘብ ለግንባታ ዝግጅት ወይም በየጊዜው ለግንባታ የሚያስፈልገው መጠን እንዲለቀቅ ሲጠየቅ የመልቀቅ፤

4. በኅብረት ሥራ ማህበር አማካይነት ተደራጅተው በልዩ ልዩ ምክንያት የህብረት ሥራ ማህበሩ ቢፈርስ ወይም የአባላት መተካካት ሲኖር በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰንና ሲጠየቅ አደራጁ በሚልከው የውሳኔ ሀሳብ ባንኩ ባለው አሰራር መሰረት የመፈጸም፤

5. ስለ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴና ሌሎች ወቅታዊ መረጃዎችን አደራጅቶ ይይዛል፤ በሚመለከተው አካል ሲጠየቅም መረጃ የመስጠት፡፡

15. የመረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ ስርዓት

1. ቢሮው እና ኤጀንሲው የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ተደራጆችን ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በሃርድና በሶፍት ኮፒ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ይይዛሉ፤
2. በቢሮውና በኤጀንሲው መካከል የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ከሁለቱም ተቋማት ሠራተኛ ውጭ በሆነ ባለጉዳይ ወይም ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ ምስጥራዊነቱን በጠበቀ መልኩ ይከናወናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም የመረጃ ልውውጥ ይደረጋል፤

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. ስለ ክልከላ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው ዝርዝር መረጃ ውጪ በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር መመዝገብና እንዲደራጅ ማድረግ የተከለከለ ነው፤
2. ከአደራጁ ውጭ ማንም ሰው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን መመዝገብና ማደራጀት የተከለከለ ነው፤
3. አንድ የህብረት ስራ ማህበር አባል ካሉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ አይችልም፤በየትኛውም ፕሮግራም ከአንድ ጊዜ በላይ ከተመዘገበ ከሁሉም ፕሮግራሞች እንዲሰረዝ ይደረጋል፤
4. አንድ የህብረት ስራ ማህበር አባል በየትኛውም የቤት ልማት ፕሮግራም

ላይ በራሱም ሆነ በትዳር አጋሩ ሥም ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ አይፈቀድም፤

5. በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ሥም የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ያለው ወይም ኖሮት ከ1997 ወዲህ ለሦስተኛ ወገን በሽያጭም ሆነ በስጦታ ያስተላለፈ በህብረት ስራ ማህበር መደራጀትና መመዝገብ አይቻልም፤
6. በወቅቱ ያልተመዘ ገበና አባላቱን አሻራ እንዲሰጡ ያላደረገ የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤትህብረት ሥራ ማህበር እንዳልተደራጀ ይቆጠራል፤
7. ፍቃደኛ ሆኖ በጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ የነበረ የማህበር አባል ወደ 2005 ዓ/ም ምዝገባቋት ውስጥ መመለስ አይችልም፡፡

17. ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

1. በምዝገባና በማደራጀት ሂደት ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ተመዝጋቢ ቅሬታውን በጽሁፍ ለአደራጁ አካል ቅሬታ ያደረበት ድርጊት ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤
2. ቅሬታ የቀረበለት የሥራ ክፍል ለቀረበለት ቅሬታ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል፤
3. በስራ ክፍሉ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ተገልጋይ ጉዳዩን ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ያቀርባል፤ኮሚቴውም የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
4. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በመመርመር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤
5. ተቋሙ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕዝብ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ጽህፈት ቤት ወይም ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤

18. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

19. ስለተጠያቂነት

1. ይህን መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም የመንግስት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በወንጀል፣በፍትሐብሔር እንዲሁም በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. ይህን መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው በወንጀል ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ወይም በሁለቱም ተጠያቂ ይሆናል፤

20. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

26. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ ኤጀንሲው ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

27. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስአበባ

ግንቦት 10/2015 ዓ.ም

አቶ ግዛቸው አሊ

የአዲስ አበባ ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

አባሪ-1

የቤቶች ግንባታ ዋጋ ግምት ሠንጠረዥ ለመጀመሪያ ዙር ምዝገባ የቀረበ (በየሩብ ዓመቱ ሊቀየር የሚችል)

ተራ ቁጥር	የህንፃው ዓይነት	የቤቱ ስፋት በሜ/ካሬ		የአንድ ሜ/ካሬ ዋጋ	ጠቅላላ የቤቱ የግንባታ ዋጋ
1	G+4	60	ባለ አንድ መኝታ	7,998	479,880
		75	ባለ ሁለት መኝታ		599,850
		105	ባለ ሶስት መኝታ		839,790
2	G+7	60	ባለ አንድ መኝታ	9000	540,000
		75	ባለ ሁለት መኝታ		675,000
		105	ባለ ሶስት መኝታ		945,000
3	B+ G+9	60	ባለ አንድ መኝታ	12,061.90	882,086.75
		75	ባለ ሁለት መኝታ		1,104,025.71
		105	ባለ ሶስት መኝታ		1,547,300.53
4	2B+G+13	60	ባለ አንድ መኝታ	13,086.82	926,023.38
		75	ባለ ሁለት መኝታ		1,157,529.23

		105	ባለ ሶስት መኝታ		1,620,540.92
5	2B+G+15	60	ባለ አንድ መኝታ		900,000
		75	ባለ ሁለት መኝታ		1,125,000
		105	ባለ ሶስት መኝታ	15,000	1,575,000

ቅጽ-2

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ

በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ

1. የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ፡--

   የመኖሪያ ቤት ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ (**በአደራጁ አካል የሚሞላ)**

2. የአመልካች ሁኔታ፤-

   2.1. ስም ---------------------- የአባት ስም ------------------ የአያትስም--------------------

   ፆታ -------- እድሜ-----------------

   2.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------ የእናት አባት ስም ------------------------

   የእናት አያት ስም -----------------------

   2.3 የትዳር ሁኔታ

   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች☐ በፍቺ የተለ የ/☐ በሞት የተለየ/☐

   2.4. ያገባ/ች ከሆነ የትዳር አጋር ስም ከነአያት --

   2.5. የአመልካች መኖሪያ አድራሻ፡-

   ከተማ-------------ክ/ከተማ------------------------ወረዳ ------የቤት ቁጥር-----------

   የቤት ስልክ ቁጥር-----------------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር----------------

ኢሜል አድራሻ--------------------------------

መታወቂያቁጥር፡-------------------------------

የቀበሌ……………………የመ/ቤት………………(የፓስፖርት)ቁጥር--------------

2.6. የአመልካች የእንቅስቃሴ አካል ጉዳት ካለሁኔታውይገለጽ---------------------------------

----

3. የስራና የገቢ ሁኔታ

3.1. የስራ ሁኔታ፤-

የመንግሥት ☐ መንግስታዊ ያልሆነ☐ የግል ተቀጣሪ☐ በግል ስራ☐

3.2. የስራ አድራሻ

የመ/ቤቱ ስም-----------------------------------የሚገኝበት ከተማ------------ክ/ከተማ-----

ወረዳ----------------ስልክ ቁጥር------------------ኢሜል አድራሻ------------ፖ.ሣ.ቁ.------

1.3 የአመልካች የወር ገቢ መጠን በብር -------------/------------------------------------

4.የሚፈልጉት የክፍል ብዛት

ባለ 1 መኝታ☐ ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ☐

5. የሚመርጡት የህንጻ ከፍታ(ለመጀመሪያ ዙር የቀረበ አማራጭ)

G+4 ☐ G +7 ☐ B +G+9 ☐ 2B+G+13 ☐ 2B +G+15 ☐

6. የሚኖርበት / የምትኖርበት ቤት ሁኔታ፡-

የቀበሌ☐ የኪራይ ቤቶች☐ ደባልጥገኛ☐ ከግለሰብ ኪራይ☐ በሌላ☐

7.የምዝገባ ቁጥር 40/60------------------------------ ወይም የ20/80 ----------------------

8. እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

8.1. ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ፣

8.2. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በራሴም ሆነ በትዳር አጋሬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ ወይም ኖሮኝ ከ1997 ዓ.ም. ወዲህ በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ መሆኑን፤

8.3. ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የሚጠበቅብኝን የቤቱን ግንባታ ዋጋ 70 በመቶ በተፈቀደው ባንክ በዝግ ሂሳብ የማስቀምጥ መሆኑን፤

8.4. በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፤

8.5. እኔም ሆነ የትዳር አጋሬ የምንኖረው በመንግስት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ቤቱን በተረከብኩ በ30 ቀን ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ

መሆኔን፤

8.6. በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ ቤቱ ከመገንባቱ በፊት ከሆነ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑን፣ ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ለመሆን የምስማማ መሆኑን፤

8.7. ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን፤

8.8. የጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያሟላሁ በመሆኑ ህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፤

የጋራ /ህ/መ/ቤ/ህ/ሥ/ማ/ አባሉ ሙሉ ስም---------------------ፊርማ ------------ቀን -----------
-

<u>በአደራጅ ባለሙያ የሚሞላ</u>

የባህር መዝገብ ምዝገባ ቁጥር------------------------

የሰራተኛው ስም ------------------ ፊርማ ------------- ቀን----------------

ቅጽ አረጋጋጭ ስም -------------------------- ፊርማ-------ቀን--------------

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵውንና ትውልደ ኢትዮጵውያንን በጋራ ህንፃ የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ

ቅጽ -2

1.የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ--------------------------የጋራ ህ/መ/ቤትኃ/የተ/የህ/ስ/ማ

2. የአመልካች ሁኔታ፣

2.1. ስም ------------------- የአባት ስም -------------------- አያት ስም -------------------------

ፆታ ------- ዕድሜ------- ዜግነት-------------የፓስፖርት ቁጥር-------------

2.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------ የእናት አባት ስም -----------------------

----የእናት አያት ስም------------------------------

2.3 የመኖሪያ አድራሻ

2.3.1 አገር--------------------------------------

2.3.2 ከተማ------------------------------------

2.4 የትዳር ሁኔታ

ያገባ/ች☐ ያላገባ/ች☐ በፍቺ የተለ የ/ች☐ በሞት የተለ የ/ች ☐

2.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም ----------------- የአባት ስም ------------------

የአያት ስም-------------------

3.የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት

ባለ 1 መኝታ☐ ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐

4.የተወካይ መረጃ፤

4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት---

4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ፡---

- ክልል----------------------------- ከተማ--
- ዞን/ክ/ከተማ----------------------------- ወረዳ -----------------------------
- ቀበሌ ----------------------------- የቤት ቁጥር ----------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር --------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ------------------------

5 እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

5.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

5.2 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩኝ እና በቤት ልማት ፕሮግራም ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

5.3 እኔም ሆነ የትዳር ጓደኛዬ የምንኖረው በመንግስት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ቤቱን በተረከብኩበ 30 ቀን ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.4 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የሚጠበቅብኝን የቤቱን ግንባታ ዋጋ 70 በመቶ በተፈቀደው ባንክ በዝግ ሂሳብ የማስቀምጥ መሆኑን፤

5.5 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.6 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ ቤቱ ከመገንባቱ በፊት ከሆነ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑን እና ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ለመሆን የምስማማ መሆኑን፣

5.7 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም፣

5.8 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያሟላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-------------------------------------

ፊርማ --------------------------------

ቀን ---------------------------------

<u>በአደራጅ ባለሙያ የሚሞላ</u>

የባህር መዝገብ ምዝገባ ቁጥር-------------------------

የሰራተኛው ስም ------------------ ፊርማ ------------- ቀን----------------

ቅጽ አረጋጋጭ ስም -------------------------- ፊርማ-------ቀን--------------